# የተከበረን ሞት

ብገዛ ተጠቃሁ
ብታገል ድል ነሳሁ
ጠላትን አሳፈርኩ
አሜን ብል ተዋረድኩ
እምቢ ብል ተከበርኩ ፡፡
በአምጽ ነጻ ወጣሁ
ወገኔን አስኩራሁ
አገርን አስከበርኩ
ከሃዲንም ታዘብኩ ፡፡

ሰማዕታትን ዘከርኩ
አደራ ጠብቄ ቃል-ኪዳን አከበርኩ
ታሪክ ያከበረው ያ ክቡር አጽማቸው
እስከ ምጽዓቱ እንዲቆይ ገናና ስማቸው
አኩሪ ታሪካቸው ፤ መልካም ዓርዓያቸው
ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ሲውደስላቸው ፤ ሲከበርላቸው
ያ ምሥዋዕታቸው፤ ያ ጀግንነታቸው ፤ ቆራጥነታቸው
ዘለዓለም ይቆያል በታሪክ መዕራፍ ፤ በክብር ቦታቸው
ሲከበር ይኖራል በተስውለት ሕዝብ በኢትዮጵያ ሀገራቸው ፡፡
ብናገር ተሰማሁ
ዝም ብል ተረሳሁ
ብጠይቅ ተረዳሁ
ባልጠይቅ ደነቆርኩ
ብፈራ ተዋረድኩ
ብደፍር ተከበርኩ
ሙብቴን አስከበርኩ
ነጻነት አስመለስኩ ፡፡

ለመኖር ስል አልኖርኩ
ልቆይ ብየ አልቆይሁ
ሞት ፈርቼ አልሸሽሁ
በዕበላ ባይነት ህሌናየን አልሸጥኩ
በህሌና መኖሬ ምንኛ ተጥቀምኩ
የራሴ ሰዉ ሆኘ ሞቴን መርጫለሁ፡፡

ከህሌና ትዝብት ከአዕምሮ ወቅሳ
ከሰብዕና ውርደት ከመንፈስ ጠባሳ
ይሻላል መበደር ሞትን ከአባ ታጥቅ ካሳ
ከዚያ ሞት ኣይፈሬ ከመቅደላ አንብሳ ፡፡
ከአልኩ ባይ ማሽቃበጥ ከአጎብጓቢ ስግደት
ካሾክሿኪ ቅጥፈት ከውስዋሳ ቅሌት
ከዕለት ፍርፋሪ ከጊዚያዊ ምቾት
ታሪክን አዋርዶ ከማግኘ ዳረጎት
ለጌታ እግር ስሞ ከሚገኝ ምጽዋዕት
ራስን አቃልሎ ከሚመጣ ሀሴት
ይበልጣል ማግኘቱ የተከበረን ሞት

ለየካቲት ሰማዕታት መታሰቢያ
ከነዓን
የካቲት 2006